የሰ/መ/ቁ. 33470

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ - ቀረበች

**ተጠሪ፡-** መገርሳ ጉደታ - ከጠበቃ ሻለቃ ሃይሉ ቦረና ጋር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሽርክና ውልን መሰረት ያደረገ የንብረት እና የገንዘብ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ናት፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተችውም በሞት የተለየው ባልዋ እና ተጠሪ በጋራ አቋቁመው ሲሰሩበት ከነበረው ጋራዥ ከተገኘው ገቢ ድርሻዋን እንዲከፍላት ወይም የጋራዡን ግማሽ እንዲሰጣት በመጠየቅ ነው ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ጋራዡ የግሉ እንደሆነ፣ከአመልካች ባል ጋር አድርገውት የነበረው ውል የሽርክና ሳይሆን የደባልነት እንደሆነ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክሱን የሰማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ እና በአመልካች ባል መካከል የተደረገ የሽርክና ውል የለም በማለት ወስኖ የነበረ ቢሆንም፤ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽርክና ውል መኖሩን በማረጋገጥና በመወሰኑ በጉዳዩ ስረ- ነገር ላይ ክርክሩ ቀጥሎአል፡፡ በመጨረሻም የእሽሙር ሽርክና ውል ተደርጐ ነበር ቢባልም፤በአመልካች ባል ሞት ምክንያት ፈርሶአል፡፡ የሽርክና ውሉ ተዋዋዮቹ ይዘውት የመጡትን ንብረት እንጂ ጋራዡን አይመለከትም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረበችውን የገቢና የጋራዥ ድርሻ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሽርክና ውል አለ እየተባለ የአመልካች የገንዘብ ክፍያ እና የንብረት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በተጠሪ እና በአመልካች ባል መካከል የእሽሙር የሽርክና ውል እንደነበር በፍ/ቤት ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ ይህን በተመለከተ በአሁኑ ደረጃ የሚባል ነገር የለም፡፡ በዚህ ደረጃ ሊወሰን የሚገባው ነጥብ የዚህ ውጤት ምንድነው የሚለው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለፀው ተዋዋዮቹ ውሉን ሲያደርጉ በየግላቸው የነበሩዋቸውን መሣሪያዎች ይዘው መግባታቸውን በውሉ ላይ በግልጽ በማስፈር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም የጋራዡን ንግድ ሥራ በጋራ ለማቋቋም ውል አላደረጉም፡፡ በየግላቸው የነበሩዋቸውን መሣሪዎች በመያዝ ሥራ የሚሰሩበት ጋራዥ በተጠሪ ይዞታ ስር እንደሆነና የሚታወሰውም በሱ ስም ብቻ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በንግድ ሕግ ቁ.271 እንደተመለከተው የእሽሙር ማህበር ማህበርተኞቹ እንደፈቃዳቸው የውላቸውን ሁኔታዎች ወስነው የሚያቋቁሙት እንደመሆኑ በተያዘው ጉዳይም ተዋዋዮቹ በሚያመቻቸው መንገድ ወስነው እንዳቋቋሙት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በንግድ ሕግ ቁጥር 273 እንደተደነገገው ደግሞ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር እያንዳንዱ ማህበርተኛ ገቢ ላደረገው መዋጮ ባለሃብትነቱን እንደያዘ

ነው የሚቆየው። ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እንደሚታየው ውሉ ከተደረገ በኋላ በጋራ የተገዛ ንብረት ወይም የተደረገ መዋጮ የለም። ይልቁንም የጋራዥ ንግዱ በተጠሪ ስም ብቻ እንደተመዘገበ ነው የቀጠለው። የንግድ ፈቃዱም በተጠሪ ስም ነው። በመሆኑም የአመልካች ባለቤት የጋራዡም የጋራ ባለሃብት ነው የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም። ሲጠቃለል አመልካች በጋራዡ ላይ የጋራ ባለሐብትነት መብት እንዳለ በመቁጠር ያቀረበችው ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው።

ቀጥለን የተመለከትነው ሌላው ነጥብ ሟች እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ያለውን የትርፍ ክፍያ እና የሽርክና ውሉ በተደረገበት ጊዜ ይዘዋቸው መጣ የተባሉትን መሣሪያዎች በሚመለከት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የውሳኔውን ክፍል ነው። አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበችው አቤቱታ ጭምር እነዚህን ነጥቦች በማንሳት ተከራክራለች። የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው አመልካች በትርፉም ሆነ በመሣሪያዎቹ ላይ መብት እንዳላት ግንዛቤ ተወስዶአል። ከዚህ ባለፈ ግን በጠየቀችው ዳኝነት መሰረት ይህ ይገባሻል ወይም አይገባሽም የሚል ውሳኔ አልተሰጠም። ስለዚህም በዚህ ረገድ ሊታረም የሚገባው ስህተት እንዳለ ለመገንዘብ ችለናል። ስህተቱ ይስተካከልም ዘንድ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05140 ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48762 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል።
2. አመልካች ከባለቤትዋ ሞት በኋላ ያለውን ትርፍ እንድትካፈል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም። ጋራዡን ግማሽ ልካፈል በማለት ያቀረበችውም እንደዚሁ ተቀባይነት የለውም ብለናል።
3. የሽርክና ውሉ በሟች ምክንያት እስከፈረሰበት ቀን ድረስ ለነበረው ጊዜ የተገኘ ትርፍ ካለ አመልካች የመካፈል መብት አላት። ሟች ለሽርክና ማህበሩ በመዋጮነት ገቢ ያደረጋቸው መሣሪያዎች ካሉም ሊመለሱላት ይገባል። ተጠሪ በእነዚህ መሣሪያዎች በመጠቀም ያገኘው ገቢ ካለም እንደዚሁ ተጣርቶ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል። ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩ በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በእነዚህ ሦስት ነጥቦች ግራ ቀኝ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል። ይፃፍ።
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

    መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ኃ